የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

መስከረም 24/2003

<u>የሕዝብን መብት መርገጥና በፈሰሰ ደሙም መቀለድ ያብቃ!</u>

የኢትዮጵያን ሕዝብ መብት በመርገጥና በመጣስ የሚታወቀውና ሁሌም የሚወገዘው የወያኔአገዛዝ በቀይ ሽብርና በሕዝብ ፍጅት ተከሰው የነበሩ 16 የደርግ ባለስልጣናትን ዛሬ ከቃሊቲ እስር ቤት ለቋል፡፡ ሌሎችም የእስር ጊዜያቸው " 20 ዓመት ሲሞላ ይለቀቃሉ" ሲልም አስታውቋል፡፡ ኢፖእአኮ ይህን በመለስ አገዛዝ የተወሰደ እርምጃ ሕገ ወጥ ብሎ እያወገዘ የሕዝብን መብት መንጠቅና በፈሰሰ ደሙም በዕብሪት መቀለድ ነው ሲል ይነቅፈዋል፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለጠው የመለስ አገዛዝ ራሱ በቀይ ሽብር በተለይም በመቀሌ የአስተማሪ ማህበር መሪዎችና ተማሪዎችን በማስገደል የተጫወተው የነፍስ ግድያ ሚና የታወቀ ሆኖእያለ ፤ ወያኔ ዛሬም የቀይ ሽብር ሰለባዎች የነበሩትን ኢሕአፓዎች እያፈነና እያደነ ባለበት፤ብዙ ሺ ሀገር ወዳዶችን በየማጎሪያው አፍኖ እያሰቃየ መሆኑ እየታወቀ፤ ለሰላምና ዕርቅ ጉባዔ የመጣውን አበራ የማነ አብን እስከዛሬም አስሮ እያሰቃየ፤ የሀገራችን የፍትህ ተቋም ነፃ ሳይሆን በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር መሆኑን ስናውቅ የመለስ አገዛዝ በቀይ ሽብር ለፈሰሰው ደም የቀርቋሪ መስሎ ያነባው የአዞ እንባ ሆነ የፍርድ ሂደት ህገወጥና ከቶም የሚደገፍ አልነበረም/አይደለምም፡፡ የወንጀሉ ዋና ተጠቂዎች ለክሱም ሆነ ለምህረቱም ጭራሹንም ድምፅ ሳይጠየቁ አፋኙ አገዛዝ ከሳሽና መሐሪ ሆኖ መሰየሙም በሕዝብ ደም ላይ ዳግም መቀለድ ነው፡፡ ያጠፉን በሕዝብ ሽንጎ፤ የተጠቁት ባሉበት ፤ የሀገር ሽማግሌዎችና  አስታራቂዎችን አሳትፎ ይቅር ይቅር መባባልን ወያኔ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስተምረው ልምድ አይደለም፡፡ ይህ ግን አልተካሄደም-- ወንጀለኞችን ማርኩ ያለው ሌላ ወንጀለኛ ነው፡፡ ይህንምህረት ለማድረግ ከሕዝብም ውክልና የለው፤ ህጋዊ መሰረትም የለው፡፡ ስለዚህም ወያኔ ዳግም የሕዝብን ዋና መብት ነጥቋል፡፡ ምህረት ጠያቂ ተብለው የቀረቡት የሀይማኖቶች መሪዎች አንዱ በተለይ የወያኔ ካድሬ ሲሆን ሁላቸውም በጥቅሉ ግን አንዲትም ቀን ወያኔ ፀረ ሕዝብ ወንጀል በሕዝብ ላይ ሲፈፅም የተቃውሞ ድምፅን በለሆሳስ እንኳን ያላቀረቡ ያላሰሙሐሳዊ መሲሆች ናቸው፡፡

ወያኔ ማርኳቸው ብሎ ከለቀቃቸው ውስጥ የቀድሞዎቹን እነ እርገጤን ዓይነቶቹን አውሬዎች ሳናነሳ በቀይ ሽብር ዋና ተጠያቂ የሆኑትን ነው፡፡ ፍቅረ ስላሴ ወግደረስ ወንጀሉ  ከመንግሥቱ አይተናነሰም፡፡ የመጋቢ ህምሳ አለቃ ለገሰንወንጀል ሁሉም ሕዝብ የሚያውቀው ነው፡፡ እንዳለ ተሰማ ከ1000 ያላነሰ ሕዝብን በብቸና( ጎጃም) አስጨርሷል፡፡ እሸቱ ሽንቁጤ የ 8 ወር ነፍሰ ጡሯን ዳሮ ነጋሽንና ( ከአረመኔው ግርማ ከበደ ጋር በመሆን ) ሌሎች (ቢያንስ) 27 ዜጎችን መግደሉ የታወቀ ነው ፡፡ ስለ ገሰግስ ገብረ መስቀል ጭራቅነት ደግሞ የአዲስ አባባ ሕዝብ መስክር ቢባል ሳምንታት አይበቁም፡፡ ወያኔ ለቀቅኳቸው ያለው እነዚህና መሰል ነፍስ ገዳዮችን ነው፡፡ ሕዝብን አላማከረ፤ አላሳተፈ፤ ከሕዝብ እሺ ይማሩ ይለቀቁን ፍቃድ አላገኘ---ግና በዕብሪት ለኢትዮጵያዊ ደም ባለው ጥላቻና ንቀት ብቻ እነሆ አውሬዎችን ለቀበት ሕዝብንም ምን ትሆን ብሏል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፈሰሰ ደሙና ለደረሰበት አሰቃቂ በደል

ወንጀለኞቹን በስርዓት እንደሚፋረድ ጥርጣሬ ባይኖረንም በዜጎች ደም የታጠቡ አውሬዎች ከእስር ተለቀው ለህገር የታገሉ የኢትዮጵያ ልጆች ዛሬም በእስር መማቀቃቸው፤ ለስየል መዳረጋቸውናደብዛቸው ጠፋ መባሉ ግን በጣም አሰቃቂ ፀረ ሕዝብ ግፍ ነው:: በደሉና ግፉ ያልደረሰባቸው፤ የቀይ ሽብር እሳት ያለበለባቸው ዛሬ በየሰገነታቸው ሆነው እሰየው ምህረት ተደረገ ቢሉ የደሙ ልቦች፤የተቃጠሉ አንጀቶቸ የሚያሽራቸውን ገና አላገኙም:: የቂም ስርም በዚህ ወንጀለኛን ወንጀለኛ እየለቀቀው ባለው ሂደት ከቶም አይነቀል:: ፍትህን ያጣ ደም ሁሌም ይጮሃል-- የንፁሃን ደም ጩኸት ደግሞ ከነጎድጓድ ይበልጣል::

ኢፖእአኮ በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ይከበሩ ዘንድ ሲታገል 16 ዓመት አሳልፏል:: ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ሲል ጮኋል:: የወያኔ አገዛዝ የቀይ ሽብር ፍርድ ወዘተ ማለትከጀመረም ጀምሮ ፈራጅም፤አሳሪም፤ መህሪም ሕዝብ እንጂ ሕዝብን እየረገጠ ያለና ራሱም በወንጀል ተካፋይ የሆነ አገዛዝሊሆን አይችልም ሲል ተቃውሟል:: የደር ግ ባለሰልጣኖችም ቢሆኑ አለፍርድ ለዓመታት መታሰራቸውን ተቃውሟል:: ወያኔ የፈፀመውን ግድያ ሁሉ አጋልጧል :: በየማጎሪያወ ያሉ ከ35 ሺ ያላነሱ ዜጎች እንዲፈቱ ሁሌም በመጮህ ላይ ነው:: ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮም በወያኔ እጅ ወድቀው ደብዛቸው የጠፋውን የኢሕአፓ መሪዎችንም አባሎችንም ስም እያነሳ የት ደረሱ ሲል መቆየቱ የሚታወቅ ነው:: ዛሬ የነዚህ ሁሉ ዜጎች ሰቆቃና ስየል ሳያበቃ፤ የነ ፀጋዬ፤ ስጦታው፤ አበራሽና ስንቶቹ ጓዶችና ዘመዶች እንባ ሳይታበስ፤ የታገቱት ሁሉ ለፍርድ ተብዬውም እንኳን ሳይበቁ በየእስር ቤቱ ሲጠበሱ ፤ ርጉዝ ሳይቀር ገዳዮችና የሰውን አካል ሲተለትሉና ሲቦጭቁ የነበሩ ጭራቆች፤ ቀይ ሽብር አፋፍሙ ብለው አዛዦች፤ የራሳቸውንም ጓደኞች ጄኔራሎችና መኮንኖች አራጆች፤አብዮታችንን ተከላከልን እንጂ ጥፋት ከቶም አላደረግንም ባይ የቀድሞ ጠቅላይ ሚነስቴሮች የደርግ መኮንኖች ተለቀው መታየቱ ወያኔና ፍትህ ፤ ወያኔና ይሉኝታ ከቶም የተቆራራጡ ጠላቶች መሆናቸውን ያረጋግጥልናል:: የሕዝብ የፍትህና የፍርድ ቀን ገና ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ አሰቃቂ ወንጀል የፈፀሙበትን ሁሉ ይፋረዳቸዋል!
ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!!

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE